# ውጭ ሆኖ የሚበላባቸውን አካባቢዎች ከሲጋራ ጪስ የፀዳ ለማድረግ

ከ22 ሴፕቴምበር 2010 ጀምሮ የሲጋራ ማጨስ ማእቀብ

## በምእራብ አውስትራሊያ ውጭ ሆኖ በሚበላባቸው አካባቢዎች ማጨስ ክልክል ነው

ቦታው ለማጨስ የተከለለ አካባቢ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ግለሰብ ውጭ ሆኖ በሚበላባቸው ሥፍራዎች ማጨስ ክልክል ነው።

**ውጭ ሆኖ የሚበላበት አካባቢ** ማለት ሕዝብ የሚጠቀምበት ቦታ ወይም በከፊል ሕዝብ የሚጠቀምበት ሲሆን፤

- በንግድ ደርጅትነት መሰረት ሆኖ፤ ግለሰቦች በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው ምግብ ወይም መጠት የሚወስዱ ከሆነና፤
- በቤት ውስጥ ያልሆነ የሕዝብ መናፈሻ ናቸው።

የሲጋራ ማጨስ ማእቀቡ ውጭ ሆኖ በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው ምግብ ወይም መጠት የሚወሰድበት ቦታ፤ ለምሳሌ ሬስቶራንቶች፤ ቡና ቤቶች፤ ትናንሽ ሱቆች፤ የምሳ መሸጫ ቦታዎችና ሌሎችም የምግብ ማቅረቢያዎች ላይ ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል።

## ፈቃድ ያላቸው መጠጥ ቤቶች

ፈቃድ ያላቸው የመጠጥ ቤት ሃላፊ የሆኑ ግለሰቦች (ባለቤት/ባለይዞታ) ነገር ግን ምግብ ለማቅረብ ፈቃድ የሌላቸው ቦታዎች፤ "ቦታው የሕዝብ ሆኖ የተከለለ እስካልሆነ ድረስ"፤ እስከ 50 በመቶ የሚሆነውን ውጭ ሆኖ የመብያ የመጨሻ ቦታ ሊያደርጉት ይችላሉ።

ፈቃድ ያላቸው የመጠጥ ቤት **"የመጨሻ አካባቢ"** ማለት፤

- ቦታው የመጠጥ ቤት ፈቃድ ተፈጻሚ የሚሆንበት ካልሆነ፤
- ቦታው ውጭ ሆኖ የሚባላበት ካልሆነና
- ከአጠቃላይ የቦታ ይዘቱ፤ ውጭ ሆኖ የሚባላበት ቦታ ከ50% የማይበልጥ ከሆነ ነው።

በማንኛውም ጊዜ፤ የሚጨስባቸውን እና የማይጨስባቸውን ቦታዎች በግልጽ መለየቱን የሚያረጋግጥ ተገቢ እርማጃ መውሰድ ያስፈልጋል። ይህም ማለት፤ በሁለቱ ቦታዎች መካካል ያለው ድንበር ከሁለቱም ስፍራዎች ለግለሰቦች ግልጽ ሆነው መታየታቸውን ማረጋገጥ ነው።

ፈቃድ ያላቸው የመጠጥ ቤት ባለቤቶች/ባለይዞታዎች በተቻለ መጠን በንግድ ቦታዎቻቸው፤ ውጭ ሆኖ የሚበላባቸውን ቦታዎች ጨምሮ፤ ደንበኞቻቸው ለትንባሆ ጪስ እንዳይጋለጡ እንዲያደርጉ ይበረታታሉ። ፈቃድ ባላቸው ይዞታዎቻቸው ማጨስ ጨርሶ የተከለከለ ለማድረግም መምራጥ ይችላሉ።

## ፈቃድ ባላቸው መጠጥ ቤቶች የሚደረጉ ምልክቶች

ማጨስ የተከለከለባቸው ቦታዎች ሁሉ፤ በቂ የሆነ ቁጥር በመጠቀም፤ ምልክቶች መለጠፍ አለባቸው፤ በተጨማሪም፤ መግቢያዎች ላይና ማጨስ በተከለከለባቸው ቦታዎች ለግለሰቦች በግልጽ ሊታይ በሚችል አይነት መለጠፍ አለባቸው።

ከላይ በተጠቀሰው አይነት፤ "ማጨስ አይቻልም" ወይም "ማጨስ ክልክል ነው" ወይም ማጨስ ክልክል ነው ይሚለውን ምልክት መለጠፍ ያስፈልጋል።

ማእቀቡን በተመለከተ መልክቱን ለመስተላልፍ እንዲያመች፤ የጤና ክፍል ተገቢ የሆኑ ምልክቶችን ለንግድ ቤቶችና ለአካባቢ መንግሥታት ያቀርባል።

## ፈቃድ ያላቸው መጠጥ ቤቶች ሠራተኞች

- ፈቃድ ያላቸው መጠጥ ቤቶች ሠራተኞች በሚጨስባቸው ስፍራዎች አገለግሎት እንዲሰጡ መገደድ የለባቸውም፤ ግሊጋሎት አንስጥም በማለታቸውም ከሥራ ሊባረሩ አይችሉም።

HP 11901 OCT'10

## ተፈጻሚነት

- ውጭ ሆኖ የሚበላባቸውን ቦታዎች አስመልክቶ ማጨስ መከልከሉን ተፈጻሚ ማድረግ የአካባቢ መንግሥት ሃላፊነት ነው።
- የአካባቢ መዘጋጃ ቤቶች፤ የከባቢ የጤና መኮንኖችን ወይም ተጨማሪ መኮንኖችን፤ ለምሳሌ ሬንጀርስ በመቅጠር አዲሱ ደንብ ተፈጻሚ እንዲሆን እንዲረዳ ማድረግ ይችላሉ፤

ይህንን ጉዳይ አጽንኦት መስጠት ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም ደንቡ ሲደነገግ የህዝብ ከፍተኛ ድጋፍ ነበረው። ካለፉት ልምዶች እንደምንረዳው፤ አብዛኛዎቹ የምእራብ አውስትራሊያ ኗሪዎች ደንቡን ተፈጻሚ እንደሚያደርጉት ይጠበቃል።

## መቀጮ

ውጭ ሆኖ በሚበላባቸው ቦታዎች የሲጋራ ማጨስ ደንብን በተላለፈ ግለሰብ ላይ የሚከተሉት መቀጮዎች ይጣሉበታል፤

| | |
|---|---|
| በፍርድ ቤት የሚጣልው ከፍተኛ መቀጮ | $2000 |
| ደንብ የመተላለፍ ማስጠንቀቂያ | $300 |

## የባለቤት/የባለይዞታ ሃላፊነቶች

ባለቤት/ባለይዞታ የሆነ ግለሰብ ውጭ ሆኖ በሚበላባቸው ቦታዎች ግለሰቦች ካጨሱ፤ ባለቤቱ/ባለይዞታው ደንቡን እንደጣሰ ይቆጠራል። ባለቤት/ባለይዞታ ጥፋተኛ ያለመሆኑን ለመከላከልና ለማረጋገጥ፤

- ደንቡ ለመጣሱ እርገጠኛ  አለመሆናቸውን፤ ወይም
- ደንቡ መጣሱን ካወቁ፤ ግለሰቡ እንዳያጨስ ተገቢውን እርምጃ መውሰዳቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

ባለቤቶች/ባለይዞታዎች ተገቢወን እርመጃ ወስደዋል ለማለት የሚከተሉትን ማድረግ ይኖርባቸዋል፤

- ግለሰቡን ደንብ መተላለፉን መግለጽ፤
- ከዚያም ሲጋራውን እንዲያጠፋና ጨፍልቆ እንዲጥለው መጠየቅ፤
- ግለሰቡ ይህንን ለመድረግ ፈቃደኛ ካልሆነ፤ ሲጋራ ማጨሱን እስኪጨርስ ድረስ  ምግብ ከሚበላበት ቦታ እንዲሄድና እንዲጨርስ መጠየቅ ናቸው።

ለተጨማሪ መረጃ የትንባሆ ቁጥጥር ቅርንጫፍ ቢሮን ያነጋግሩ፤

ስልክ ቁጥር: 1300 784 892

ኢሜል: tcb@health.wa.gov.auFor more

**Disclaimer:**
The information contained in this factsheet has been produced as a guide only.
To view the full details in the relevant Tobacco Control legislation,
visit www.health.wa.gov.au/tobaccocontrol